



# <u>የሀገሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ ያለህ!!!</u>

በኢትዮጵያ ታሪክ ዘመናት በነገሥታት፣ በመሳፍንት፣ እንዲሁም በካህናት (ጳጳሳት) ሲታወሱና ሲጠሩ ስናስተውልው የነበረ እውነታ ነው። በአንጻሩ ዘመናት በሕዝብ ሲሰየሙና ሲታወሱ የተስተዋለበት ወቅት የለም። በዘንድሮው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ የአገራችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘመንን በራሱ የሚያስጠራበት ሁኔታ እየተከሰተ ይገኛል። በዛሬው ዕለት ማለትም ግንቦት ፲፭ ቀን ፳፻ወ፪ ዓ.ም. (May 23rd, 2010) በተደረገው ፬ኛ አገራዊ ምርጫ ከሌላው ጊዜ በበለጠ የሕዝብን የበላይነት ሊረጋገጥበት የሚችል ክስተት ሲሆን ለዚህም ገዢው ፓርቲም ሆነ ተቀናቃኝ የፓለቲካ ፓርቲዎች በመስማማት ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ ስላደረጉት ጥረት ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። ከነሱ የበለጠ ደግሞ የአገራች ሕዝብ በምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ በመገኘት ድምጹን በመስጠት ላሳየው አስደናቂ ተግባር ሊመሰገንና እንኳን ደስ ያለህ ሊባል ይገባዋል። *የእግዚአብሔር ሕዝብ አይደል*?